# የፈጠራ ጥሪ – በኢትዮጵያ የህፃናት ክትባት እና የክትባት ተደራሽነት ለማነቃቃት እና ለማሳደግ ሲባል በህፃናት አድን ድርጅት የተጀመረ አዲስ መርሃግብር



*Hanna Adcock / Save the Children*

ከዓለም የክትባት ሳምንት  በተገናኘ፣ የአለም የህፃናት አድን ድርጅት በጂኤስኬ በተገኘ የአንድ ሚሊዮን ዶላር የገንዘብ ድጋፍ በኢትዮጵያ እና ናይጄሪያ  የሚገኙ ሀገር በቀል ድርጅቶችን ለማጎልበት እና ህጻናት ክትባት እንዳይወስዱ ከሚያደርጉ ረጅም ጊዜ የቆዩ እንቅፋቶችን ለመቅረፍ ፈጣን መፍትሄ ለማፈላልግና ለመስጠት ንቅናቄ ጀምሯል። በመሆኑም የ *Save the Children Immunisation Accelerator* ከማህበረሰብ አቀፍ ድርጅቶች፣ ከሀገር በቀል እና ከአለም አቀፍ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ከምርምር ቡድኖች፣ ከማህበራዊ ኢንተርፕራይዞች እና ከቴክኖሎጂ ኩባንያዎች አዳዲስ የፈጠራ ሃሳቦች የያዙ ማመልከቻዎች ለመቀበል ዝግጁ ነው። ከማመልከቻዎቹ ውስጥም ተስፋ ሰጪ ተብለው የሚታሰቡ አካሄዶች ተመርጠው ተጽኖአቸውን በመጨመር እና ፈጠራዎቻቸውን በ 'ፓይለት እስኬል' ደረጃ እንዲሰሩ ለማድረግ የገንዘብ እና ቴክኒካል ድጋፍ የሚያደርግ ይሆናል።

አህጉራችን አፍሪካ በዓለም 'ዜሮ ዶዝ' ህፃናት ከሚገኙባቸው አህጉራት በቁጥር ከፍተኛውን ደረጃ ይይዛል - ይህም ማለት መደበኛ ክትባት ወስደው የማያውቁ፡ 8.7 ሚሊዮን ህፃናቶች አሉ ማለት ነው፡፡ ከእነዚህ ህፃናት ውስጥ ከአንድ ሦስተኛ በላይ የሚሆኑት የሚኖሩት በናይጄሪያ እና ኢትዮጵያ ውስጥ ሲሆን፤ በወረርሽኝ፣ በድህነት፣ በየአየር ንብረት ለውጥ፣ በአለመረጋጋትና ግጭት እና ተያያዥ ምክንያቶች የክትባት  መርሃግብር  እየተስተጓጎሉ ይገኛሉ። በባለፈው አመት የአለም የህጻናት አድን ድርጅት (ሴቭ ዘ ችልድረን) እና ጂኤስኬ ለአስር አመታት የዘለቀው ትብብራቸውን በማደስ ከጂኤስኬ በተገኘ 15 ሚሊየን ፓውንድ ኢንቨስትመንት በኢትዮጵያ እና በናይጄሪያ የዜሮ ዶዝ ህፃናትን ቁጥር በመቀነስ ላይ ያተኮሩ ሁለት አዳዲስ የክትባት መርሃ ግብሮችን ጀምሯል።

ከእነዚህ ምርሃ ግብሮች ጋር በተያያዘ የ *Immunisation Accelerator* የክትባት አቅርቦትን እና አጠቃቀምን በተመለከተ ማንኛውንም አይነት ከክትባት ጋር ተያያዘ የሆኑ እንቅፋቶችና ማነቆችን የሚፈቱ የፈጠራ ስራዎችን ማወዳደር ይፈልጋል፤ ይህም ለምሳሌ የማህበረሰብ ተሳትፎን ማሻሻል፣ የክትባት አቅርቦትን እና ተደራሽነትን በማቀላጠፍና ማጠናከር እና የክትባት ሽፋን ሁኔታዎችን  ዉሳኔ ለመስጠት የሚአስችል የመረጃ አያያዝ ሊያካትት ይችላል፡፡

በዚህም መሰረት የተለያየ መጠን ላላቸውን የሱቪል ማህበረሰች ድርጀቶች  (startups) ፍላጎቶችን ለማሟላት የተዘጋጀ ደጋፍ ሲሆን በፕሮጀክት እስከ 100,000 ዶላር የሚደርስ የገንዘብ እንዲሁም ከቴክኒካል ድጋፍ እስከ የሕግ ምክር እና የምርት ስም (branding) እገዛ ድረስ ያጠቃለለ የድጋፍ አገልግሎት የሚስጥ መርሃ ግብር ነው ።

**የኢፌዲሪ ጤና ሚኒስቴር የክትባት አገልግሎት ዴስክ ኃላፊ አቶ መልካሙ አያሌው እንዲህ ብለዋል፡-**

"በአሁኑ ወቅጥ፣ ሙሉ በሙሉም ሆነ በከፊል የመከተብ እድል ያላገኙ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ህጻናት በመኖራቸው ፣ የኢፌዲሪ ጤና ሚኒስቴር  ያሉትን ተግዳሮቶች ለመፍታት፣ ባለቤትነትን ለመፍጠር እና የህብረተሰቡን ተሳትፎ ለማሳደግ ሀገር አቀፍ መፍትሄዎችን እና ፈጠራዎችን ለማበረታታት ጥረት ያደርጋል። "

**የአለም የህጻናት አድን ድርጅት በኢትዮጵያ (ሴቭ ዘ ችልድረን ኢንተርናሽናል) ጊዜያዊ ዳይሬክተር መሀመድ ዳሂር እንዲህ ብለዋል፡-**

"የህጻናት አድን ድርጅት (ሴቭ ዘ ችልድረን) Immunization Accelerator (የክትባት አፋጣኝ) የክትባትን ተደራሽነትን የሚፈታተኑ መሰናክሎች መፍትሄ የሚሆኑና በአገር ውስጥ የሚመሩ፣ አዳዲስ መፍትሄዎችን ለመፍጠር የሚረዳን ትልቅ እድል ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ክትባት ያልጀመሩና ጀምረው ያላጠናቀቁ  ህጻናትን ለመድረስ እየተካሄደ ያለውን ጥረትም ያግዛል።"

**የጂኤስኬ ዋና ዳይሬክተር የሆኑት ዶ/ር ቶማስ ብሬየር እንዲህ ብለዋል፡-**

"ለክትባት አፋጣኝ (Immunization Accelerator) የሚመጡ ማመልከቻዎችን ለማየት ጓጉተናል። ከሴቭ ዘ ችልድረን ጋር ያለን ትብብር በአካባቢው ማህበረሰቦች፣ ባለሙያዎች እና ባለድርሻ አካላት የሚመራ ነው፣ በመሆኑም በኢትዮጵያ እና በናይጄሪያ ያለውን ሀገር በቀል እውቀት እና አቅም መፈለግ የልጆች ክትባት እጥረት እና ተያያዥ ችግሮች ለመፍታት የሚያግዙ ልዩ ፈጠራዎችን ለማግኘት መሰረታዊ ነው፡፡ የክትባት አፋጣኝ (Immunization Accelerator) የሚያመጣቸውን አዳዲስና ትኩስ ሀሳቦች በጉጉት እንጠብቃለን በተጨማሪም ድርጅታችን ጂኤስኬ በናይጄሪያ፣ ኢትዮጵያ እና ከዚያም በላይ ያሉ የህጻናትን የወደፊት ህልወና አቅጣጫ ለመቀየር የሚረዱንን ፈጠራዎች ወደ ፍጻሜ እንዲመጡ አስፍላጊውን ለማድረግ ዝግጁ ነን።

ማሳሰቢያ፡ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ፕሮጀክቶች በፈጠራ ዑደቱ የሙከራ ደረጃ ላይ የሆኑ እና የክትባት እንቅፋት እንዴት እንደሚፈቱ የሚያሳይ ማስረጃ ማሳየት የሚችሉ መሆን አለባቸው። እያንዳንዳቸው በጠንካራ የምርጫ መስፈርት የሚገመገሙ ይሆናል፡፡

በ www.stc-accelerator.org ላይ ያመልክቱ እንዲሁም የበለጠ ይወቁ; እስከ ግንቦት 16 ቀን 2016 ዓም ድረስ ማመልከት ይቻላል፣ ከዚያም በ2017/2025 ለሁለተኛ የፈጠራ ጥሪ ይካሄዳል።

የዓለም ጤና ድርጅት መረጃ
ፎቶዎችን እዚህ ያውርዱ.

**ለበለጠ መረጃ**


ምዕራፍ ሰሎሞን፣ የክትባት ፕሮግራም ዳይሬክተር፣ ሴቭ ዘ ችልድረን ኢትዮጵያ (**የአለም አቅፍ የህጻናት አድን ድርጅት በኢትዮጵያ**)። ኢሜል:mirafe.solomon@savethechildren.org

ኢዳ ዘካርያስ (ወ/ት)፣ አድቮኬሲ፣ ካምፔን፣ ኮሙዩኒኬሽን እና የሚዲያ ዳይሬክተር ሴቭ ዘ ችልድረን ኢትዮጵያ (**የአለም አቅፍ የህጻናት አድን ድርጅት በኢትዮጵያ**)። ኢሜል: edda.zekarias@savethechildren.org


ስለ **የአለም አቅፍ የህጻናት አድን ድርጅት በኢትዮጵያ** (ሴቭ ዘ ችልድረን)
የአለም አቅፍ የህጻናት አድን ድርጅት እያንዳንዱ ህጻን የሚገባውን የወደፊት እድል እንዲያገኝ ለመርዳት የተቋቋመ ድርጅት ነው። ዩናይትድ ኪንግደምን ጨምሮ ከ100 በሚበልጡ አገሮች ህጻናት ደህንነታቸው የተጠበቀ፣ ጤናማ እና መማር እንዲችሉ መሆናቸውን እናረጋግጣለን። ለአንድ ምዕተ-አመት, ለህፃናት መብት ቆመናል እና ድምፃቸው እንዲሰማ አረጋግጠናል።

ከልጆች ጋር, ለልጆች, የወደፊቱን ጊዜ የተሻላ ለማድረግ እንሰራለን

ለበለጠ መረጃ www.savethechildren.org.uk ን ይጎብኙ

ስለ GSK
ጂኤስኬ ሳይንስን፣ ቴክኖሎጂን እና ተሰጥኦን አንድ ለማድረግ ዓላማ ያለው ዓለም አቀፍ የባዮፋርማ ኩባንያ ነው።
gsk.com/company ላይ የበለጠ ያግኙ።